# ከፍተኛና አስቸኳይ ማስጠንቂያ ለአማራ ሕዝብ!!!

ከሰሞኑ ወያኔ በአህዮቹ  ብአዴን፣ ኦሕዴድና ቤጉዴፓ (የቤንሻንጉል ጉምዝ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ) በኩል ለአማራ ሕዝብ ከፍተኛ እልቂት ደግሷልና አማራ ሆይ ተጠንቀቅ!!! "ተነቃብን!" ብለው ካልተውት በስተቀር ይሄንን ደግሰውልሀል!!!

እልቂቱ ሊፈጸም የታቀደው እንዴት መሰላቹህ፦ እንደምታስታውሱት ሰሞኑን በተከታታይ መተከል ላይ ስለተፈጸመብን የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ብአዴንም ሆነ አጠቃላይ አገዛዙ የነበረው አቋም "አማራ ተለይቶ አልተጠቃም፣ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ጥቃት ሳይሆን ግጭት ነው!" የሚል ነበረ፡፡ የቤተመንግሥቱ አውደልዳይ አህያ የብአዴን ሊቀመንበር አቶ ደመቀ መኮንንም ቦታው ድረስ ሔዶ ከተመለሰ በኋላም ያንጸባረቀው አቋም ይሄንኑ ነበረ፡፡ ሌሎች የብአዴን ባለሥልጣናትም ይሄንኑ እንዳሉ ሰምታቹህቸዋል!!!

"ለውጥ መጣ!" ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማጃጃል መቀሌ ተቀምጦ ሀገሪቱን ፍጹም ታማኝ ባሮቹና አህዮቹ በሆኑት ኦሕዴድና ብአዴን በኩል እየገዛ ያለው ወያኔ ከታች የምገልጽላቹህን ሴራ ስላሴረ ግን ከትናንት ጀምሮ ብአዴንን በድንገት "አማራ ተለይቶ አልተጠቃም፣ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ጥቃት ሳይሆን ግጭት ነው!" የሚለውን አቋሙን እንዲቀይርና መግለጫ በማውጣት ጭምር "የዘር ማጥፋት ጥቃት ተፈጽሟል!" ብሎ እንዲያስታውቅ አድርጓል!!!

ይሄም ብቻ አይደለም ከእንግዲህ በኋላ በአማራ ላይ ጥቃት ቢፈጸም ወደቦታው ኃይል የሚያዘምት መሆኑንም ጭምር እንዲዝት አድርጎታል፡፡ ቁልፉ ነገር ያለው እዚህ ላይ ነው እንግዲህ፡፡ አሁን ሊደረግ የታሰበውን ሴራ ልንገራቹህ፦

አገዛዙ ሰሞኑን ቤንሻንጉል ጉምዝ ውስጥ በአማራ ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ ከዚያ "ከእንግዲህ አንታገስም!" ብሎ እንዲፎክር የተደረገው ብአዴን "ጨፍጫፊዎቹን ለመደምሰስ!" በሚል ፋኖንና የአማራን ወጣት አስታጥቆ ወደ ቤንሻንጉል ጉምዝ እንዲያዘምት ይደረጋል፡፡ ከዚያ ይሄንን የዘመተውን የፋኖና የአማራ ወጣት መከላከያ ተብየው አሽባሪ የወያኔ ኃይል "በሉዓላዊ ክልል ላይ ወረራ ፈጽማቹሀል፣ ንጹሐንንም ጨፍጭፋቹሃል!" ብሎ ተቀብሎ ለመረፍረፍ ነው የተዘጋጁት!!! ይሄንንም ተከትሎ አማራንና አልፎም እንዲህ የሚያገለግሉትን አህዮቹን የብአዴን ባለሥልጣናትንም ጭምር የሚበላ እርምጃ ለመውሰድ አገዛዙ ተዘጋጅቷል!!!

ልብ በሉ ፋኖና የአማራ ወጣት ጭፍጨፋ ስለፈጸመ እንዳይመስላቹህ መከላከያ "ንጹሐንን ጨፍጭፋቹሀል!" ብሎ የሚጨፈጭፋቸው፡፡ ጉምዞች የጨፈጨፉት አስመስሎ አማራን የሚጨፈጭፈውም፣ በጉምዞች ላይ የበቀል እርምጃ የተወሰደ አስመስሎ ጉምዞችን የሚጨፈጭፈውና በዚህ አሳቦም ፋኖንና የአማራ ወጣትን የሚጨፈጭፈውም ሁሉንም የሚያደርገው አገዛዙ ነው!!!

ጆሮ ያለህ ስማ!!!

አገዛዙ ለዚህ ሠላሳ ዓመት ለቆየ እራሱ ለሠራው ችግር መፍትሔ ማምጣት ከፈለገ መፍትሔው ይሄ ሳይሆን አንደኛው መፍትሔ ጠንቀኛው የጎሳ ፌዴሬሽን ከዚህች ሀገር እስኪወገድ ድረስ 80% የመተከል ነዋሪ አማራ

በሆነበት ሁኔታ መተከል ወደ ቤንሻንጉል ጉምዝ ሊከለል የሚችልበት ምንም ዓይነት አግባብ የለምና መተከልን ወደ አማራ ማድረግ ሲሆን፡፡ ሁለተኛው የመፍትሔ እርምጃ ደግሞ በተቀረው የቤንሻንጉል ጉምዝ ያሉ "የክልሉ ባለቤቶች ናቸው!" ከተባሉት ውጭ ላሉ ወገኖቻችን የክልሉ ሕገመንግሥት ተሻሽሎ "የአማራ ክልል ሕገመንግሥት!" እንደሚሉት ሕገመንግሥት ለሁሉም ነዋሪ ዕኩል መብት የሚሰጥና የፖለቲካ ውክልና እንዲያገኙ የሚፈቅድ ማድረግ ብቻ ነው!!!

ከዚህ ውጭ ያሉ እርምጃዎች ሁሉ የውሸትና ምንም ዓይነት መፍትሔ ማምጣት የማይችሉ ሽፍጠኛ እርምጃዎች ናቸው!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው